# አዋጅ ቁጥር ......../2008

## የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ......../2008

የኢትዮጵያ የዱር ህይወት ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም እንዲሁም የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓት አያያዝን በህብረተሰቡና በባለድርሻ አካላት ተሳተፎ በማጎልበት እየደረሰባቸው ካለው ከፍተኛ አደጋ እንዲያገግሙ በማድረግ የዱር ሕይወት ሃብትን በተገቢ ሁኔታ መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዱር ህይውት ሀብቱን በማስተዋወቅ የመልካም ገፅታን በመገንባት ሀገሪቱ ማገግኘት የሚገባትን ምጣኔ ሃብታዊና ስነ ምህዳራዊ ጠቀሜታ የላቀ ደረጃ በማድረስ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ተወዳዳሪ የምትሆነበትን መንገድ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍል ከተፈጥሮ ሃብቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ በማድረግና የባለቤትነት ስሜቱን ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለጥበቃ ቦታዎች እንክብካቤ ሥራዎች የሚሰጠውን ድጋፍ የሚያስተባብር፣ ሥራውን የሚመራ እና የገንዘብ ምንጭ የሚያፈላልግ ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሕገመንግስቱ አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችን ፈንድ ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ......./2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጣ አዋጅ ቁጥር ----/2008 ነው፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ አዋጅ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
3. "ቦርድ"ማለት የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ልማት ፈንድ ቦርድ ነው፡፡
4. "ፈንድ" ማለት ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰብ ሆኖ በቦርዱ ውሳኔ መሠረት ጥቅም ላይ የሚውል ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ነው፡፡
3. "ሚኒስቴር" ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፡፡
4. "ባለስልጣን" ማለት የዱር ሕይወት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡
5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለፈንዱ መቋቋም

3. ***መቋቋም***

1. የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ፈንድ ከዚህ በኋላ "ፈንድ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2. ፈንዱ ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ለዚህ አዋጅ ዓላማ ማስፈፀሚያ ይውላል፡፡

4. <u>የፈንዱ ዓላማዎች</u>

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. በፌደራል መንግሥት የሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችን ለማልማትና ጉዳት የደረሰባቸው መልሰው እንዲያንሰራሩ ለማድረግ የሚያስችል ተጨማሪ ሃብት የሚገኝበትን አሰራር በመፍጠር በመንግስት ውስን በጀት ሊሸፈኑ የማይችሉ የጥበቃና የልማት ሥራዎችን መደጎም፤
2. በፌደራል መንግስት የሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችን ለማልማትና ጉዳት የደረሰባቸው መልሰው እንዲያንሰራሩ ለማድረግ በግለሰቦች፣ በቡድኖች ወይም በማህበረሰቦች ተነሳሽነትና በጎ ፈቃደኝነት የሚከናወኑ ሥራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ መደገፍና መምራት፤
3. በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚገኘውን ህብረተሰብ ዘለቄታዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፤
4. የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዝግጁነትን ማጎልበት፤
5. ፈንዱ በክልል ለሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ዓለም አቀፍ ድጋፍ በማፈላለግ እገዛ እንዲያገኙ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

5. <u>የፈንዱ ምንጭ</u>

1. የፈንዱ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ከዱር ሕይወት ጋር በተያያዘ ለፌዴራል መንግሥት የሚገባ ማንኛውም ገቢ፤

ለ. ለዱር ህይወት ልማት፣ ጥበቃና ለሌሎች ልዩ ልዩ ተመሳሳይ ተግባራት ከአገር ውስጥና ከውጪ የሚገኙ ድጋፎች፤

ሐ. በፌዴራል መንግሥት ከዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ጋር በተያያዘ ስምምነት የሚፈጸምባቸው የካርቦን ልቀት የመቀነስና ሌሎች የስነ-ምህዳር አገልግሎት ፕሮጀክቶች የሚገኝ ድጋፍ፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ለ/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በፕሮጀክት የሚገኙ ድጋፎች በፕሮጀክቱ ሰነድ ወይም ከለጋሽ አካል ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት የሚፈጸሙ ይሆናሉ፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሰው ገንዘብ ለፈንዱ ሲባል በተከፈተ የባንክ ሂሳብ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተቀማጭ ይደረጋል፡፡ ፈንዱ የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሣብ ይኖረዋል፡፡

6. <u>በፈንዱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

1. በፈንዱ ተጠቃሚ የሚሆን ተቋም ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 13(5) መሠረት የፈንዱ አጠቃቀምን በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ አዘጋጅቶ በሚኒስቴሩ ያጸድቃል፡፡

7. <u>ስለ ፈንዱ ሂሳብ</u>

1. ጽህፈት ቤቱ የፈንዱን ሂሳብ በሚመለከት ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2. የፈንዱ ሂሳብ በየዓመቱ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚሰየሙ በውጭ ኦዲተሮች ይመረመራል፡፡

3. የሂሳብ ምርመራዎችና ሌሎች የፋይናንስ ዘገባዎች በቦርዱ ተቀባይነት አግኝተው በፀደቁ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ይደረጋሉ፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለፈንዱ አስተዳደር

8. **መቋቋም**

1. የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ፈንድ ጽሕፈት ቤት ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ እራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል፡፡

9. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የጽህፈት ቤቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ፣ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

10. **የጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር፤**

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቦርዱ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤
2. የፈንዱን ሂሣብና ሪከርድ ይይዛል፤
3. የቦርዱን ሥራ አመራር የስብሰባ ሪኮርዶችን ይይዛል፤
4. ተቀባይነትና ህጋዊነት ካላቸው ምንጮች ሁሉ ገንዘብና ሌሎች የገንዘብ ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች ያፈላልጋል፤

DRAFT

5. ቦርዱ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ከፈንዱ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ሆነው ለተገኙ የሥራ ፕሮግራሞች ገንዘብ ይመድባል፣ ያከፋፍላል፣
6. የፈንዱ ተጠቃሚ የሥራ ፕሮግራሞችን የዕቅድ ክንውን አፈጻጻማቸውን ይከታተላል፣ በየሩብ አመቱ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፣
7. የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችን መልሶ ማቋቋም እና የማልማት ሥራዎችን ይደግፋል፣
8. ሕብረተሰቡን በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች እንክብካቤ ተግባራት እንዲሳተፍ በቦርዱ ውሳኔ መሰረት ድጋፍ ያደርጋል፣
9. በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስትሩ ሪፖርት ያቀርባል፣
10. የንብረት ባለቤት ይሆናል ፣ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ፣ይከሰሳል፣
11. ቦርዱ ያጸደቀለትን በጀት በሥራ ላይ ያውላል፡፡

11. <u>የጽሕፈት ቤቱ አቋም</u>

ጽሕፈት ቤቱ፡-

1. ቦርድ፣
2. በቦርዱ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል፡፡

12. <u>ስለቦርዱ አባላት</u>

1. ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በሚኒስቴሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፡፡
2. የቦርዱ አባላት ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያያዥነት ካላቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ሲቪክ

ማህበራት እንዲሁም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተውጣጡ ይሆናሉ፣ ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

## 13. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ፈንዱን በተመለከተ የሕግ ረቂቅ እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
2. ፈንዱን በበላይነት ያስተዳድራል፤
3. የፈንዱ ገቢዎች በወቅቱ መሰብሰባቸውን እና በፈንዱ ሂሳብ መግባታቸውን ያረጋግጣል፤
4. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በፈንዱ ለመጠቀም የሚያስችሉ መመዘኛዎችን ያወጣል፤
5. በፈንዱ የተመደበውን ገንዘብ ለማግኘት ብቁ ሆነው የተገኙ የሥራ ፕሮግራሞችን ያፀድቃል፤
6. በፈንዱ የሚደገፉ ፕሮግራሞች በጀት ውስጥ ቢያንስ 30 በመቶ ለልማትና ጥበቃ አጋዥ የሆኑ የህብረተሰብ አቀፍ ስራዎች ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
7. የፈንዱን የእቅድ ክንውን አፈጻጸምና ኦዲት ሪፖርቶች ይገመግማል፤ በሪፖርቶቹ መሠረት ተገቢ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፣
8. ፈንዱ ሊያድግ የሚችልበትን መንገድ ያፈላልጋል፤
9. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ያፀድቃል፤
10. የፈንዱን ዓላማዎች ለማስፈጸም አግባብነት ያላቸውን የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ አካላት፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የትምህርት ተቋማትና ለጋሽ ድርጅቶች መካከል ትብብር እንዲኖር አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፤

DRAFT

11. ፈንዱ በጥበቃ ቦታዎች የሚኖሩና የሕብረተሰብ አካላት ተጠቃሚነትን የሚያሳድጉ የልማት ተግባራት መከናወናቸውንና የተቋቋመበትን አላማ እያሳካ መሆኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡

14. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ መደበኛ ስብሰባውን በሦስት ወሩ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፣
3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት በአብላጫው ድምጽ ሲደገፍ ነው፣ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፣

15. <u>የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ከቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽቤቱን ሥራዎች ያቅዳል፣ ይመራል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን የጽህፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፣
3. የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሰረታዊ ዓላማዎች በመከተል የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
4. የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
5. ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

DRAFT

6. ጽሕፈት ቤቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤

7. የፈንዱን የሥራ እንቅስቃሴዎችና የፋይናንስ ይዞታ በተመለከተ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፤

8. ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

9. ለጽህፈት ቤቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

10. ከሥራ ውጭ ሆኖ በከፊል ውክልና ሲሰጥ ውክልናው ከ30 ቀን የሚበልጥ ከሆነ በቅድሚያ ለቦርዱ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

16. <u>በጀትና የኃላፊነት መጠን</u>

1. የጽህፈት ቤቱ በጀት በአንቀጽ 5 (1) ከተዘረዘሩት የፈንዱ ገቢዎች ይሆናል፤
2. የጽህፈት ቤቱ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን ይሆናል፡፡
3. የጽህፈት ቤቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

17. <u>ስለሂሳብ መዛግብት አያያዝ</u>

1. ጽህፈት ቤቱ ትክክለኛና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብትን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር ይይዛል፤
2. የጽህፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡ የኦዲተሩ የምርመራ ውጤት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ይቀርባል፡፡

DRAFT

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

18. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

19. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡

20. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከ .....................ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ..........ቀን 2008 ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዝዳንት

DRAFT

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

ለክብርት ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የትረስት ፈንድ የሕግ ማዕቀፍ ረቂቅ መላክን ይመለከታል፤</u>

በኤፌድሪ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ላለፉት ሁለት ዓመታቶች ሲያከናውነው በነበረው ጥናት መሠረት የትረስት ፈንድ የሕግ ማዕቀፍ ረቂቅ የተዘጋጀ ሲሆን ሠነዱ በሚኒስቴር መ/ቤቱና በኢፌድሪ ፍትህ ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሠጥበት ተደርጓል፡፡

በመሆኑም ይህ የሕግ ማዕቀፍ በታህሣሥ 2006 ዓ/ም ተጠናቆ እንዲቀርብ እቅድ የተያዘለት ስለሆነ አገር አቀፍ የውይይት መድረክ ከመዘጋጀቱ በፊት አስተያየት እንዲሠጥበትና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በበላይ አመራሩ በኩል ውይይት እንዲደረግበት በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>አባሪ፤</u>

- የትረስት ፈንድ ማብራሪያ 5 ገፅ
- የትረስት ፈንድ የሕግ ረቂቅ 7 ገፅ
- በፍትህ ሚኒስቴር የተሠጠ አስተያየት 8 ገፅ

<u>ግልባጭ</u>፡-

- ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
- ለ SDPASE ፕሮጀክት

<u>ኢ.ዱ.ል.ጥ.ባ</u>

DRAFT